**EthioLion**

# ኢትዮጵያን ከወያኔ መንጋጋ ለማላቀቅ ትግላችን በየፈርጁ ይቀጥላል አድማው በካናዳም ተጀምሯል !

ኢትዮጵያን በጎሳና በቋንቋ ከፋፍሎ፣ ሕዝብን ከሕዝብ አጋጭቶና አለያይቶ፣ አገራችንን አስገንጥሎና 80 ሚሊዮን ሕዝብ ወደብ አልባ አድርጎ በጠመንጃና በከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲው 17 ዓመት ሙሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ የተቀመጠው የወያኔ ኢሕአዴግ ቡድን በምርጫ 97 የኢትዮጵያ ሕዝብ አልፈልግህም ብሎ በምርጫ ቢያሸንፈውም ወያኔ በመሳሪያ ኃይል ምርጫውን ሰርቆና አጭበርብሮ ሲያበቃ ሕዝብን በመግደል፣ በማሰርና የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን በቃሊቲ በማጎር አሻፈረኝ ብሎ አምባገነን አገዛዙን ቀጥሏል።

ዛሬ ደግሞ ዳር ድንበራችንን ለጎረቤት አገር አሳልፎ በመስጠት የአገራችንን ሉዐላዊነት ከማስደፈሩም በላይ ዜጎቻችንን ቁም ስቃያቸውን እያሳየ ይገኛል፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን በረሃብ አለንጋ ሲረግፉ እየተመለከተ "ረሃብ የለም" በማለት ዓለምን ለማታለል ሲሞክር ይሰማል። አገራችንን ምስቅልቅሏን እያወጣ የህገሪቱን ሀብት በጥቂት ግለሰቦችና ፍርፋሪ ለቃሚዎቹ ስር በማድረግ የኑሮው ሁኔታ ገጠሩ ከተሜው መቋቋም ቀርቶ የሚቀምሰው በማጣት በሞትና በጣር ላይ ይገኛል። በሌላ በኩል ደግሞ በተዘረፈው ሀብትና ንብረት የወያኔ ባለሥልጣኖች ሕንጻዎችን በመኮልኮል፣ የንግድ ተቋማቱን በመቆጣጠር፣ ሀብት ወደ ውጭ አገር በማሸሽ ተጠምደው "አገራችን አደገች" "ለማች" እያለ የተራበውን ሕዝባችንን ሲያሾፍበትና ሲቀልድበት ይሰማል። ስለወያኔ ማንነትና ተግባር የኢትዮጵያን ሕዝብም ሆነ ዓለም በሙሉ ያወቀው ስለሆነ ተዘርዝሮም አያልቅ። ማንሳት የተፈለገበት ዋና ምክንያት እንዴት በውጭ ዓለም ያለነው ለትግሉ እገዛ እናደርጋለን የሚለውን ለመዳሰስና በቆራጥነት ለመታገል ጊዜው መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

ወያኔ በሀገራችን ብቻ ሳይሆን በውጭ ያለውን የንግድ ተቋም ደግሞ ለመቆጣጠር እየተሯሯጠና በእድሜ ቀጣዮቹ ሆዳሞችና የወገን ጠላቶች አማካኝነት የዘረጋውን ገመድ መበጣጠስ ይኖርብናል።

በቅርቡ በአሜሪካ የተጀመረው የወያኔን የንግድ ውጤቶችና ተቋማትን በማንኛውም ዘርፍ ላይ የተሰማራውን ያለመግዛትና ያለመጠቀም አድማ በማድረግ ራስ ምታት የሆኑበትን በመከተል፣ በካናዳም፣ በአውሮፓም፣ በአውስትራሊያም ሆነ በአፍሪካ ለማካሄድ ሰፋ ያለ እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

በዚህም መሰረት በካናዳ በተለይም በትላልቅ ከተሞች ማለትም በቶሮንቶ፣ ኦታዋ፣ ሞንትሪያል፣ ካልጋሪ፣ ቫንኮቨር በመሳሰሉት ከህገር ቤት በሚመጡ እቃዎች፣ የምግብና የመጠጥ ውጤቶች፣ ቁሳቁስ እና አገልግሎቶች ባለመጠቀም ጸረ ወያኔ ትግላችንን ማፋፋም አለብን።

ግልጽ መሆንና መታወቅ ያለበት ወያኔ በተለያዩ ግለሰቦችና የንግድ ተቋማት ስም ንግዱን ስለሚያካሂድ እከሌ ወይም እከሊት ወያኔ አይደለም ወይም አይደለችም ብሎ መታለል የለብንም። ከኢትዮጵያ በሚመጡ ማንኛውም ፕሮዳክትስ ላይ አድማ ሲደረግ በአጠቃላይ ነው። እንደዚሁም የወያኔን ፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ሆነው በየሬስቶራንቶቻቸው የወያኔን ቴሌቪዥን ጣቢያ በማስተላለፍ እንዲሁም የወያኔን የንግድ ማስታወቂያ የሚያስራጭቱን ቴሊቪዥን፣ ጋዜጣ፣ ሬዲዮ ሁሉ ሁለቴ እንዲያስቡ እናሳስባለን። የተለያዩ የኮሚኒቲዎችን ማህበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ እንዲሁም የሙያ ማህበራት ውስጥ ተሰግስገው ወያኔያዊ ተልዕኳቸውን እየተወጡ የሚገኙትን፣ ወደ አገር ቤት እየተመላለሱ በመነገድ እዚህ ያሉትን ወገኖች በወያኔ የንግድ መስመር ውስጥ ለመክተት የሚሯሯጡትን፣ ቦታ ተመሩ፣ ንግድ ክፈቱ እያሉ የሚደልሉትን፣ በየንግድ መደብሮቻቸው በጫት መቃሚያ ቦታ የወያኔን መልዕክት የሚያስተላልፉትን ሁሉ ማንነታቸውንና ሥራቸውን በማጋለጥ ስማቸውንና የንግድ ተቋማቸውን ይፋ የምናደርግ መሆኑን እንዲያውቁት እናስጠነቅቃለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እያለቀና እየተራበ፣ እየተገደለና በግፍ እየተገዛ የወያኔን እድሜ ለማራዘምና ፍርፋሪ ለማግኘት የሚራወጡት ግለሰቦች ከወያኔ ነፍሰ ገዳዮች ተለይተው የሚታዩበት ምክንያት የለም። ስለሆነም በካናዳም በየትኛውም ከተማና ቦታ የወያኔን የንግድ ውጤቶች ላይ ማለትም የገንዘብ መላኪያ መንገዶች፣ ቢራ፣ ዋይን፣ ቅቤ፣ እንጀራ፣ ዲቪዲና ሲዲ፣ ጫት፣ አየር መንገድ፣ የቴሊቪዥን ስርጭት፣ የወያኔ ደጋፊ ምግብ ቤት፣ ሥጋ ቤት፣ እና መደብር፣ አገር ቤት የተሰሩ ፊልሞች፣ ልብሶች ወዘተ.... ላይ አድማ ስለተጀመረ የኢትዮጵያን ጠላት በገንዘባችን ማክበርና እድሜ ማራዘም ማቆም አለብን። እንደ አሜሪካ ከተሞች ውጤታማ እንደምንሆን ሙሉ ተስፋ አለን። ትግላችን ይቀጥላል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

በካናዳ የሚገኙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን

**Ethiopia Will Prevail!**